# ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የተላለፈ ቃለ ውግዘት።

በሀገር ውስጥም ሆነ በመላው ዓለም የምትገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ምእመናንና ምእመናት ሐዋርያዊት፣ ጥንታዊት፣ ታሪካዊትና ብሔራዊት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በረጅሙ የታሪክ ጉዞዋ በሃይማኖት መሪዎቿ መንፈሳዊ ብርታት፣ በሊቃውንቶቿ ትምህርት፣ በካህናቶቿ አገልግሎትና በምእመናኗ ጽንዐ ሃይማኖት ህልውናዋና አንድነትዋ ተጠብቆ መኖሩ ሁሉም የሚያውቀው ሐቅ ነው ።

ይህ ለዘመናት ተጠብቆ የኖረውን ሃይማኖቷ፣ አንድነትዋና ቀኖናዋ ለመፈታተን የሚፈልጉ የውስጥና የውጭ መናፍቃን በየጊዜው የጥፋት ሙከራ ቢያደርጉም ሃይማኖተ ጽኑ በሆነ ሕዝቧ ጥንካሬ በየጊዜው መክሸፉ ታሪክ ያስረዳል ።

በአሁኑ ጊዜም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል ፣ ከእኔ ጋርም የማያከማች ይበትናል (ማቴ 12. 13) በማለት የገለጸውን የአጽራረ ቤተ ክርስቲያን በታች ተግባር የሚፈጽሙ ከሐዲዎች ቤተ ክርስቲያንን ከምትወደው ሕዝብዋ ፣ ሕዝቡንም ከሚወዳት ቤተ ክርስቲያኑ ሊለያዩ ሆን ብለው በመነሣት የእግዚአብሔርን ቃል ፣ የሐዋርያትን ሲኖዶስ፣ የአበውን ሃይማኖት፣ ሕገ ቤተ ክርስቲያንንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በመጻረር አይሆንላቸውም እንጂ ከሆነላቸው ሊከፋፍሏት ደፋ ቀና እያሉ ይገኛሉ ።

እነዚህ ከሐዲዎችና ፀረ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል ‹‹ዘይሴሰይ እክልየ አንሥአ ሰኮናሁ ላዕሌየ›› "እህሌን የሚበላ ተረከዙን አነሣብኝ" እንደተባለው ቤተ ክርስቲያናችን አስተምራ፣ መዓርግ ሰጥታ፣ በረከቷን መግባና ተንከባክባ ያሳደገቻቸው ነበሩ፤ ነገር ግን የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ሲሳናቸው የነካቸው ሳይኖር ሀገራቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን እየካዱ ወደ ውጭ አገር በመኮብለል የክህደት ተረከዛቸውን አነሡባት።

ይህ አድራጎታቸው ወዲያውኑ ውግዘት የሚያስከትል መሆኑ በሐዋርያት ሲኖዶስ የተረጋገጠ ቢሆንም ንሥሐ ገብተው ይመለሱ ይሆናል በሚል ተስፋ ለተወሰኑ ወራት ቅዱስ ሲኖዶስ በትዕግሥት ጠብቆአቸው ነበር። ይሁንና ሌላ ተጨማሪ ክሕደት በቤተ ክርስቲያን ለመፈጸም መንቀሳቀሳቸው ሲረዳ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስና ከሐዋርያት በተሰጠው ሲኖዶሳዊ ሥልጣን የቤተ ክርስቲያኗን ሕግ ለማስጠበቅ ሲል፣

1. አባ ዜና ማርቆስ
2. አባ ኤልያስ
3. አባ ጎርጎርዮስ
4. አባ መልከጼዴቅ ይባሉ የነበሩት ጳጳሳት ረስጠብ 11 "አንድ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ጳጳስ መንበሩንና ሀገረ ስብከቱን ትቶ ወደ ሌላ ሀገረ ስብከት ይሄድ ዘንድ አይገባም" እንደዚሁም ኒቅያ 24 ‹‹ኤጲስ ቆጶሳት ከሀገረ ስብከታቸው ወደ ሌላ ሀገር ቢሄዱ ከስድስት ወር የበለጠ አይኑሩ፣ ችግር ሳይገጥማቸው፣ ሊቀ ጳጳሳቱም ሳይፈቅድላቸው ከዚህ የበለጠ ቢኖሩ ወይም ሀገረ ስብከታቸውን ትተው በሌላው ሀገር በዓለ ትንሣኤን ቢያከብሩ ከሹመታቸው ይሻሩ›› በሚለው የሐዋርያት ሲኖዶስ ሕግ መሠረት የጵጵስና ሥልጣናቸውን ሽሮ የጵጵስና ስማቸውም አንሥቶአል፤ ከዚህ ቀን ጀምሮ እነኝህ ሰዎች ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የሐዋርያት ሕገ ሲኖዶስ መሠረት የተሻሩ በመሆናቸው ምንም ዓይነት ሥልጣነ ክህነት ለመስጠት አይችሉም፣ ቢሞክሩም በማናቸውም መንገድ በሕገ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው ግልጽ ነው ።

በሌላ በኩል የቀድሞ ዐራተኛ ፓትርያርክ የነበሩት አባ መርቆሬዎስ በራሳቸው ጥያቄ ሕመም ካደረብኝ ብዙ ቀን ሆኖኛልና የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር እንዳይበደል ቅዱስ ሲኖዶስ ሥልጣኑን እንዲረከበኝ ብለው ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ሥልጣናቸውን ካስረከቡ በኋላ ቅዱስ ሲኖዶስ በአዲስ አበባ እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተወስነው እንዲኖሩ ውሳኔ አሳልፎ ነበር፤ይሁንና አባ መርቆሬዎስ በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 5 ቁጥር 138 ‹‹ከበጎች (ምእመናን) የተለየህ ብትሆን ጠላታቸው አንተ ነህ፤ የእግዚአብሔርም ባለጋራው ነህ፤ እግዚአብሔር ጠባቂ የሆናቸውን በጎች (ምእመናን ) የምታጠፋ አንተ ነህ" የሚለውን ሕገ ሲኖዶስ በመጣስ ማንም ሳይያሳድዳቸው ከምእመናን ተለይተው አገርንና ቤተ ክርስቲያንን ከድተው ወጥተዋል።

ይህም አልበቃ ብሎ የፓትርያርክነት ሥልጣናቸውን በራሳቸው ጥያቄ ካስረከቡበት ቀን ጀምሮ ተራ ሰው መሆናቸውን እያወቁ  በሌላቸው መንበርና ሥልጣን የጵጵስና ሥልጣናቸው በሕገ ቤተ ክርስቲያን ከተሻረና ስማቸው ከተነሣ ተራ ሰዎች ጋር በመሆን የሐሰት ሲኖዶስ አቋቁሜአለሁ በማለት ምእመናንን ሲያጭበረብሩ ቆይተዋል።

ይህ ሁሉ ሆኖም አንድ ቀን ንስሐ ገብተው ይጸጸቱ ይሆናል በሚል ጽኑ ትእግስት ቅዱስ ሲኖዶስ ለረጅም ጊዜ ታግሶአቸው ነበር፤ ሆኖም ንስሐ ሊገቡ አልቻሉም፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነትና ሰላም በተደጋጋሚ የቀረበላቸውን ጥሪም አልተቀበሉም።

በመጨረሻም ጭራሹኑ ለይቶላቸው ሃይማኖትን በማፍረስ፣ ሕገ ሲኖዶስን በማፋለስና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በመጣስ በሌላቸው ሲኖዶሳዊ ሥልጣን ጥር 13 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰሜን አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ እንደዚሁም ጥር 20 ቀን 1999 ዓ.ም. በቶሮንቶ ካናዳ 13 የሚሆኑ የሐሰትና የጥፋት ሕገ ወጥ ኤጲስ ቆጶሳትን ሹመዋል።

በዚህም የክሕደት ድርጊታቸው በሐዋርያት ሲኖዶስ ድስቅ 34 "ኤጲስ ቆጶስ በሦስት ኤጲስ ቆጶሳት ይሾም ዘንድ እናዛችኊለን፤ የችግር ዘመን ቢሆን እንኳ በሁለት አጴስ ቆጶሳት ይሾም፣ በአንድ ኤጲስ ቆጶስ ሊሾምላችሁ አይገባም፣ የሁለትና የሦስት ምስክርነት የጸና ይሆናልና፣ ረስጣ 58 አንድ ኤጴስ ቆጶስ ብቻው የሾመ ከሆነ ይሻር" የተባለውን ጥሰው ሁለትና ሦስት ይቅርና አንድ ሕጋዊ ኤጲስ ቆጳስ ሳይኖር ኢ- ሕጋዊ የሆነ ሢመት ሰጥተዋል።

እንደዚሁም በሐዋርያት ሲኖዶስ ረስጣ 34 " ባለ ሀገረ ስብከቱ ሳይፈቅድለት ከሀገረ ስብከቱ ውጭ ካህንን የሾመ ቢኖር ይሻር የሚለውን በመጣስ ሥልጣነ ክህነትን ሰጥተዋል።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕገ ሲኖዶስ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ከሥልጣኑ የተገለለ ፓትርያርክ በቀኖና ተወስኖ በገዳም ይቀመጣል፣ በገዳም አልቀመጥም በቀኖናም አልወሰንም በማለት እምቢተኛ ከሆነ ግን ተወግዞ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ይለይ" የሚለውን ሕግ ተላልፈው ተገኝተዋል።

አባ መርቆሬዎስና የእርሳቸው ተከታይ የሆኑ ሕገ ወጥ ሰዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትን ለማፍረስ የሚያደርጉት የጥፋትና የክሕደት ተግባር በዚህም አላበቃም፣ የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ወላዲተ አምላክ ከሆነችው እናታቸው ከቅደስት ድንግል ማርያም ነጥለው ከፀረ ማርያሞች በረት ለመክተት ካላቸው እኩይ ዓላማ በመነሣት ውዳሴ ማርያም፣ መልክአ ውዳሴና መልክአ ሥዕል እንዳይደርስ፣ ተአምረ ማርያም እንዳይነበብ፣ የሐዋርያት አመክንዮና ቅዳሴ ማርያም እንዳይቀደስ፣ ከቅዳሴ መጻሕፍት ውስጥም ዐሥራ አንዱ በሙሉ እንዳይጸለይባቸው፣ የቅዱስ ያሬድ ዜማ አሮጌና አሰልቺ ስለሆነ አገልግሎት ላይ እንዳይውል፣ የቅዳሴ ጸሎት በፒያኖ፣ በኦርጋንና በመሳሰሉት ዘመናዊ

መሣሪያዎች እንዲቀደስ፣ ያለ ጽላት ቅዳሴ እንዲቀደስ በማድረግ የቅድስት ድንግል ማርያምንና የተዋሕዶ ሃይማኖትን ክብር ተዳፍረዋል፡፡ ይህ ሁሉ የክህደትና የኑፋቄ ግንብ እየተገባ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ቤተ ክርስቲያኗን የሚመራ ቅዱስ ሲኖዶስ ነገሮችን በትዕግሥት የሚያልፋቸው ሆነው አላገኛቸውም፡፡ በመሆኑም እንደነዚህ ያሉ ከሐድያንን አስመልክቶ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በ1ኛ መልእክቱ ምዕ. 2 ከቁጥር 18-19 " ልጆቼ!! ይህቺ የመጨረሻ ሰዓት ናት፣ እኛም የመጨረሻዋ ሰዓት እንደሆነች አወቅን ተረዳን ፣ ከእኛ ያልሆኑ ከእኛ ዘንድ ወጥተዋልና፣ ከእኛ ጋርማ ቢሆኑ ኖሮ ከእኛ ጋር በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉም ከእኛ ዘንድ እንዳልሆኑ ይታወቁ" ፡፡ ብሎ እንዳስተማረን ከእኛ ዘንድ የወጡ እንጂ ከእኛ ጋር ያልሆኑ መሆናቸውን በሀገር ውስጥም ሆነ በመላው ዓለም የሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች በሙሉ ማንነታቸውን አውቀው እንዲለይዋቸው ቅዱስ ሲኖዶስ የሚከተለውን ቃለ ውግዘት አስተላልፏል፡፡

## ቃለ ውግዘት

1. አባ መርቆሬዎስ በራሳቸው ፍላጎትና ጥያቄ የፓትርያርክነቱን ሥልጣን ለቅዱስ ሲኖዶስ ከማስረከባቸው የተነሣ፣ የፓትያርክነት ሥልጣን እንደሌላቸው እያወቁ ተወግዘው ከተለዩት፣
   ሀ/ አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ
   ለ/ አባ ዜና በጎ ሰው
   ሐ/ አባ ገብረ እግዚአብሔር ጸጋዬ
   መ/ አባ ኃይለ ኢየሱስ ከበደ ጋር በመሆን ሁሎቹም በሌላቸው ሥልጣን ኤጲስ ቆጶሳትን ሹመናል ብለው በመንፈስ ቅዱስ ላይ በመዋሸታቸውና በመዳፈራቸው፤

2. ለሁለት ሺሕ ዘመናት ያህል በአንድነቷ ጸንታ የኖረችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሆን ብለው ለመገነጣጠል አቅደውና አስበው ሕገ ወጥ ሲኖዶስ በማቋቋም በአሜሪካና በሌሎችም አህጉር የሚኖረውን ሕዝበ ክርስቲያን በማታለል የክሕደትና የሐሳዊ መሲሕ ወይም የመናፍቅ ተግባር በመፈጸማቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ለይቷቸዋል፤

**በዚህም መሠረት** ፣

ሀ/ ሥልጣነ ክህነታቸውና መርቆሬዎስ የሚለው የመዐርግ ስም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ውሳኔ የተነሣ ስለሆነ፣ ከዛሬ ጀምሮ አባ ዘሊባኖስ ፋንታ ተብለው በቀድሞ ስማቸው እንዲጠሩ፣

ለ/ በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ አገልግሎት ዙሪያም በሕይወትም ሆነ በሞት ማናቸውንም መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳያገኙ ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ከቤተ ክርስቲያን ለይቷቸዋል፡፡

3. በነዚህ ሕገ ወጥ የተሐድሶ መናፍቃን ስብስብ ሰዎች ተሹመዋል የተባሉት ኤጲስ ቆጳሳት ተብየዎች የሐሰት ኤጲስ ቆጳሳትም ቤተ ክርስቲያናቸውን ጥለውና ክደው የሔዱ ከመሆናቸውም በላይ ለከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን መዐርግ የማያበቃ ነውርና ነቀፋ ያለባቸው፣ እንደዚሁም ሥልጣነ ክህነት በሌላቸው ሰዎች የሚሰጥ ሥልጣነ ክህነት በዓለም ውስጥ ታይቶም ተሰምቶም የማያውቅና ሢመታቸውም ከሐዋርያት ሲኖዶስና ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ በመሆኑ ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው ስለሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞታል፡፡

   ይህ ውሳኔ ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ከዲቁና እስከ ቅስና ያለው ሥልጣነ ክህነታቸው በቅዱስ ሲኖዶስ የተገፈፈና የተወገዘ በመሆኑ፣ ቤተ ክርስቲያናችን አውግዛ

ለይታቸዋለች፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ዙሪያም በሕይወትም ሆነ በሞት ማናቸውንም መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳያገኙ ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ከቤተ ክርስቲያን ለይቷቸዋል፡፡

4. እሩያን በአካል የሚለውን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የነገረ መለኮት ትምህርትን በማዛነፍ "መንፈስ ቅዱስ አካል የለውም " በማለትና በድንግል ማርያም ቅድስናና ክብር የኑፋቄ መጽሐፍ በማሳተማቸው፣ እንዲሁም በሌላው ክህደታቸው ሁሉ ተወግዘው ጽጽስናቸውና ስመ ጽጽስናቸው የተገፈፈው፣
   1. አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ
   2. አባ ዜና በጎ ሰው
   3. አባ ገብረ እግዚአብሔር ጸጋዬ
   4. አባ ኃይለ ኢየሱስ ከበደ በሌላቸው ሥልጣነ ክህነት ሕገ ወጥ ሢመት መፈጸማቸውና ፀረ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ፀረ ማርያም ሆነው በመገኘታቸው ቅዱስ ሲኖዶስ በድጋሚ አውግዟቸዋል፡፡ እንዲሁም በሕይወትም ሆነ በሞት ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳይፈጸምላቸው ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ለይቷቸዋል፡፡

## <u>በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የምትገኙ ምእምናንና ምእመናት</u>

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በ2ኛው መልእክቱ ምዕራፍ 1 ቁጥር 9-11 "ማንም በክርስቶስ ትምህርት ጸንቶ የማይኖር ቢመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፣ ምክንያቱም ሰላምታ የሚሰጠው ሰው ሁሉ የክፉ ሥራው ተባባሪ ይሆናልና" እንዳለው ከነዚህ ጋር መቀራረብ በክፉ ሥራቸው ሁሉ መተባበር ነውና የሐዋርያውን ትምህርት ተቀብላችሁና አክብራችሁ ከዛሬ ጀምሮ በሀገር ውስጥም ሆነ በመላው ዓለም የምትገኙ የሐዋርያዊቷ፣ የጥንታዊቷ፣ የታሪካዊቷና የብሔራዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፣

- ሊቃነ ጳጳሳት፣
- ጳጳሳት፣
- ኤጲስ ቆጶሳት፣
- ቆሞሳት፣
- ቀሳውስት፣
- ዲያቆናትና መዘምራን ፣
- ምእመናንና ምእመናት በሙሉ በአባ ዘሊባኖስ ፈንታ መሪነት የተሰባሰቡትን የዘመናችን የፀረ ማርያምና የተሐድሶ መናፍቃን ስብስቦች ቃላቸውን እንዳታዳምጡ፣ ትምህርታቸውንም እንዳትቀበሉ፣ ኢ-ቀኖናዊ ሥርዓታቸውን እንዳትከተሉ፣ ሥልጣነ ክህነትም ከእነሱ እንዳትቀበሉ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ከእነሱ ጋር እንዳትሳተፉ ፣ ወደ ቤታችሁ እንዳታስገቡ፣ በማዕድ ተሳትፎም ሕብረት እንዳይኖራችሁ፣ የእናት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ አውግዟል፡፡

ጥር 25 ቀን 1999 ዓ.ም.
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ